በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 331/403/08
Ref. No
ቀን 29 መስከረም 2008
Date

ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
አዲስ አበባ

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መስከረም 20 ቀን 2008 ዓ.ም. በቁጥር ታ/ክ/ቀ/5/13 በተፃፈ ደብዳቤ በአካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 41/2007 መሰረት በመመሪያው አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (3) "ለተሽከርካሪ" በተሰጠው ትርጉም እና በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት "ልዩ አውቶሞቢል" የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው አካል ጉዳተኞች እንዲያገለግል ሆነው ከተሰሩ ተሽከርካሪዎች ውስጥ አንዱ መሆኑ በግልጽ የተደነገገ ስለመሆኑና በመመሪያው "ልዩ አውቶሞቢል" ማለት ለአካል ጉዳተኞች እንዲያገለግል ሆኖ የተሰራ ባለ አራት እግር ተሽከርካሪ መሆኑና የአካል ጉዳት የሌለባቸው ሰዎች ሊያሽከረክሯቸው የሚችሉትን አውቶማቲክ ማስተላለፍያ (Cars with authomatic transmissions) ያላቸውን እና ሌሎች ዘመናዊ ተሽከርካሪዎችን የማይጨምር መሆኑን የገለፀበትን 1 ገጽ ደብዳቤ ለተገቢው አፈፃፀም የላክን መሆኑን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

ማርታ ስዩም
የጉምሩክ/ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል
ቡድን አስተባባሪ

ግልባጭ፣
- ለጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ ጉዳይ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ቡድን
  ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣
- ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
  ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣

ፀ/ሕ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
e Federal Democratic Republic of Ethiopia
nistry of Finance and Economic Development

ቁጥር ን/ፈ/ቁ/5-/13
Ref.No

ቀን 20/01/2008
Date

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ለሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
ለትራንስፖርት ሚኒስቴር
ለትራንስፖርት ባለሥልጣን
ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን
ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪን ከቀረጥና ታክስ ነጻ <u>የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ይመለከታል</u>

አካል ጉዳተኞች ለግል አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን መመሪያ ቁጥር 41/2007 ወጥቶ ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ሆኖም መመሪያውን በማስፈፀሙ ሂደት "ልዩ አውቶሞቢል" በሚል በመመሪያው ጥቅም ላይ በዋለው ቃል አተረጓጎም ላይ ልዩነቶች እየተፈጠሩ መሆኑን ከሚቀርቡልን ሪፖርቶች እና በመመሪያ ተጠቃሚ ከሆኑ አንዳንድ ሰዎች ከሚቀርቡልን ጥያቄዎች መገንዘብ ችለናል፡፡

በመሆኑም በመመሪያው አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (3) ለ"ተሽከርካሪ" በተሰጠው ትርጉም እና በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት "ልዩ አውቶሞቢል" የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው አካል ጉዳተኞች እንዲያገለግል ሆነው ከተሠሩ ተሽከርካሪዎች ውስጥ አንዱ መሆኑ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በዚህም መሠረት ከእነዚህ ውጪ ያሉ አውቶሞቢሎች በመመሪያው እንደመደበኛ አውቶሞቢሎች የሚቆጠሩ ናቸው፡፡

ስለዚህ በመመሪያው መሠረት "ልዩ አውቶሞቢል" ማለት ለአካል ጉዳተኞች ብቻ እንዲያገለግል ሆኖ የተሰራ ባለአራት እግር ተሽከርካሪ ሲሆን፣ የአካል ጉዳት የሌለባቸው ሰዎች ሊያሽከረክሯቸው የሚችሉትን አውቶማቲክ ማስተላለፊያ (Cars with automatic transmissions) ያላቸውን እና ሌሎች ዘመናዊ ተሽከርካሪዎችን የማይጨምር መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አብርሃም ተከስተ
ሚኒስትር ዴኤታ